# በሰሜን አሜሪካ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማኅበር

# AEUP SUPPORT ASSOCIATION – NORTH AMERICA

------------------------------------------------------------------------------------------

## ከኢፍትሃዊ ሀይላት ጋር እየተባበሩ ኢፍትሃዊነትን መታገል አይቻልም:- አሁንም የመኢአድ ህጋዊ ፕሬዝዳንት አቶ ማሙሸት አማረ ብቻ ነዉ

--------------------------------------------------------------------------

1-መኢአድ 483 የጠቅላላ ጉባኤ አባላት አሉት:: ከጥቅምት 28/2007 እስከ ጥቅምት 30/2007 በተካሄደዉ ጠቅላላ ጉባኤ 483 የጠቅላላ ጉባኤ አባላቱ በተሳተፉበት በ477 የጠቅላላ ጉባኤ አባላት አመራሩን መረጠ:: በዚህ ምርጫም አቶ ማሙሸት አማረ የድርጅቱ ፕሬዝዳንት ሆነዉ ተመረጡ:: ሆኖም ምርጫ ቦርድ የጠቅላላ ጉባኤዉን ዉጤት ህጋዊ ነዉ ብሎ ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆነምና ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ጥር 3/2007 ዓም እንዲጠራ ተወሰነ:: ሁለተኛዉ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲካሄድ ሲጠራ ከ483 የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ዉስጥ 425 አባላት ተገኝተዉ መሪያቸዉን የመምረጥ ስልጣን ያላቸዉ እነሱ ብቻ መሆናቸዉን አስረግጠዉ አስረዱ:: በዚህም ዉሳኔአቸዉ መሰረት የድርጅቱ ፕሬዝዳንት አቶ ማሙሸት አማረ መሆኑን በአንድ ድምጽ ወስነዉ ሄዱ::

2- ወያኔ ግን መኢአድን አንቃ ለእነ አቶ አበባዉ መሃሪ እና ዶ/ር በዛብህ አስረከበች::በዚህም አቶ አበባዉ መሃሪ አንድ ጊዜ ሌላ ጊዜ ደግሞ ዶ/ር በዛብህ የመኢአድ ፕሬዝዳንት ነኝ እያሉ ወያኔን ማገልገላቸዉን ቀጥለዋል::

3. ለዚህ የወያኔ ዉለታም የኢትዮጵያ ህዝብ (በአማራ እና በኦሮሚያ ክልል) የዛሬ አመት ህዝባዊ አመጽ ሲያደርግ መኢአድን እወክላለሁ ብሎ ዶ/ር በዛብህ ከእነ አየለ ጫሚሶ ጋር በቴለቪዥን በመቅረብ የኢትዮጵያን ህዝብ ህዝባዊ አመጽ አወገዘ:: ህዝባዊ አመጹ ወንጀል ነዉ ሲልም በወያኔ ሚዲያ ቀርቦ ተናገረ::በዚህም ዶ/ር በዛብህ የወያኔን ቡራኬ ማግኘቱን አረጋገጠ:: በዚህም ሳይበቃዉ በአማራ እና በኦሮሞ ክልል ህዝባዊ አመጹ እየተቀጣጠለ ወያኔን ከመንበሯ ሊነቅላት ሲቃረብ ዶ/ር በዛብህ ከእነ ልደቱ አያሌዉ ጋር በመሆን የተቃዋሚ ፓርቲዎች ድርድር ከኢህዴግ ጋር እናድርግ የሚል የሽፋን ካባ ይዘዉ ወደ መድረክ መጡ:: ወያኔም ዶ/ር በዛብህን ማጠናከሯን በመቀጠል ዶ/ር በዛብህ ወደ አሜሪካ እና ምዕራብ ሀገራት በመሄድ የመኢአድ ደጋፊዎችን እንዲያሰባስብ እና እንዲያጃጅል ላከችዉ:: ህዝባዊዉን እና ሰላማዊን ትግል በተመንጃ እየቀበረ: ጠንካራ ታጋዮችን ወደ እስር ቤት እየወረወረ ወያኔ ለምንድን ነዉ እነ ዶ/ር በዛብህን እና እነ ልደቱን የሚንከባከበዉ ብሎ መጠዬቅ ይገባል::አቶ ማሙሸት አማረ ወያኔ ስልጣን ላይ ከቆዬችበት 26 አመታት ዉስጥ 13 አመታቱን በወያኔ እስር ቤት እንዲያሳልፍ ወያኔ የወሰነችዉ እና ደጋግማ የምታስረዉ ምን አይነት ታጋይ ቢሆናባት ነዉ? እነ ዶ/ር በዛብህ ደግሞ ምን አይነት ታጋይ ሆነዉ ብታገኛቸዉ ነዉ ፓርቲ መምራት አለባቸዉ እያለች ፓርቲዉን በህገወጥ መንገድ ፓርቲ እየነጠቀች የምትሰጣቸዉ? ብሎ መጠዬቅ ይገባል::

ዶ/ር በዛብህ አሜሪካ ሰሙኑን ብቅ ብሎ ነበር::በዚህ አጋጣሚም ጋዜጠኛ ሀብታሙ አሰፋ በህብር ሬዲዮ ዶ/ር በዛብህን አንድ አስገራሚ ጥያቄ ጠይቆት ነበር::"አሁን የመኢአድ አመራሮች እና አባላት እስር ቤት ናቸዉ::በህጋዊነት የተመረጠዉንም የመኢአድ ፕሬዝዳንት ወያኔ እስር ቤት እያሰቃዬችዉ ነዉ:: እናንተ አሁን ምን እያደረጋችሁ ነዉ?" የሚል ጥያቄ አቅርቦለት ነበር::ዶ/ር በዛብህም በጣም ሳያፍር " አዎን ወደ 22 የሚጠጉ የመኢአድ አመራሮች እስር ቤት ታስረዉብናል" ብሎ መለሰ::እዉነታዉ ግን መኢአድ የታሰሩበት አመራሮች ቁጥር 122 መሆናቸዉ ነዉ::ዶ/ር በዛብህ ግን የመኢአድ አመራሮችን ስቃይ: መታሰር: መገደል እና መባረር ከቁብም ስለማይቆጥረዉ ስንት አመራሮች እንደታሰሩም አያዉቀም::ሌላዉ አሳፋሪ መልስ ደግሞ "አቶ ማሙሸት አማረን ፕሬዝዳንት እንዳይሆን ያገደዉ ምርጫ ቦርድ ነዉ" ብሎ ቁጭ ማለቱ ነዉ::ጋዜጠኛ ሀብታሙም ጥያቄዉን በማስከተል "እና እናንተ ምርጫ ቦርድ የሚወስነዉን ዉሳኔ ፍትሃዊ ነዉ ብላችሁ ትቀበላላችሁ ማለት ነዉ?" የሚል ጥያቄ ሲጠይቀዉ ባልሰማሁም መልስ ሳይሰጥበት በዝምታ አልፎታል:: ዶ/ር በዛብህ እና ጋዜጠኛ ሀብታሙ ያደረጉት ቃለ ምልልስ የዶ/ር በዛብህን ህገወጥ የሆነ አካሄድ አጋልጦታል:: እንዲሁም የኢትዮጵያን የተቃዋሚ ደጋፊዎች በጥንቃቄ ነገሮችን እንዲመረምሩ በርካት

እዉነቶችንም ያሳዩ አስተማሪ ቃለ መጠይቅ ነዉ::በዚሁ አጋጣሚ ጋዜጠኞች እንደ ጋዜጠና ሀብታሙ አሰፋ በመረጃ እና በእዉነት ላይ የተመሰረት እዉነተኛ ተቃዋሚዎችን ከሀሰተኞቹ የማንጠር ስራ ልትሰሩ እንደሚገባ ማሳሰብ ይገባል::

---

4. በአቶ ማሙሸት አማረ የሚመራዉ የመኢአድ ህጋዊ አመራር ምርጫ ቦርድን በአንደኛ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሶ እረትቶታል::ሆነም ምርጫ ቦርድ ጉዳዩን ለይግባኝ ወደ ከፍተኛዉ ፍርድቤት በመዉሰድ ፍርዱ ተፈጻሚ እንዳይሆን አግዶታል:: ምርጫ ቦርድ እና ወያኔ አቶ ማሙሸት አማረን በህጋዊ አካሄድ ተከራክራ መርታት እንደማትችል ታዉቃለች::እንዲሁም የአቶ ማሙሸት አማረን: የእነ ዘመነ ምህረቴን: የእነ ለገሰ ወ/ሃናን እንዲሁም በርካታ ምርጥ የህጋዊዉ የመኢአድ አመራሮችን ሰብዕና ጠንቅቃ ስለምታዉቅ ይሄን ሃጋዊ አመራር ለማሰር ከፍ ዝቅ ማለት ጀመረች::በዚህ መሃልም የምርጫ 2007 ዓም ፕሮግራም እየደረሰ መጣ:: በሂደቱም በኢ/ር ይልቃል የሚመራዉ ሰማያዊ ፓርቲ እና በአቶ ማሙሸት የሚመራዉ የመኢአድ ፓርቲ የ2007ዓም ምርጫዉን በትብብር ለማከናወን በሚስጢር እየመከሩ መሆኑን መረጃ ደረሳት::

ወያኔ ያላት ብቸኛ አማራጭ ጠንካራዎቹን የፖለቲካ ፓርቲዎች መምታት መሆኑን ወሰነች::ለ2007ዓም ምርጫ ጠንካራ እንቅፋት ሊሆኑብኝ ይችላሉ ብላ የፈረጀቸዉም መኢአድ: አንድነት እና ሰማያዊ ፓርቲ ሆነዉ ተገኙ::በተለይም መኢአድን እና ጠንካራ ህጋዊ አመራሮቹን ብትንትናቸዉን ማዉጣት: ማሰር እና መግደል አለብኝ የሚል ቁርጥ ዉሳኔ አድርጋ ለዚህ ዉሳኔዋም የሽፋን ድጋፍ የሚሰጧትን እነ አበባዉ እና እነ ዶ/ር በዛብህን አሰልፋ ተነሳች:: በማስከተለም የመኢአድ አመራሮችን እያሳደደች ማሰር: ለማሰር ያልቻለቻቸዉ ላይ ደግሞ ገንዘብ መድባ እከሌን የያዘልኝን ይሄን ያህል ብር እከፍለዋለሁ የሚል ማስታወቂ ታስነግራለች::ለምሳሌ የመኢአድ ምክትል ፕሬዝዳንት የሆነዉን አቶ ዘመነ ምህረቴን የያዘልኝን 100,000 (መቶ ሽህ ) ብር እከፍለዋለሁ የሚል ማስታወቂያ አዉጥታ የመኢአድ አመራሮችን ለማጥፋት ያላትን ቁርጠኝነት አረጋግጣለች::

ወያኔ እስካሁን ድረስ እየመረጠ ወደ እስር ቤት የሚወረዉራቸዉ እነማንን ነዉ ብሎ መጠዬቅ ብቻ በቂ መልስ ይሰጣል::ጠንካሮቹን አመራሮች እየገደለ: እያሰረ እና በልዩ ልዩ መልክ እያኮላሸ ደካማዎቹ እና የርሱ ተላላኪዎች ግን የመድብለ ፓርቲ ስርዓት እንዳለ እንዲያስመልስሉለት አሜሪካ እና አዉሮፓ ፓስፖርት እና ቪዛ እየሰጠ ያመላልሳቸዋል:: ለምሳሌ የሰሜን አሜሪካ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማህበር ለአለፉት ሶስት አመታት አቶ ማሙሸት አማረን ወደ አሜሪካ በመጋበዝ እና ለደጋፊዎች ንግግር እንዲያደር ያደረገዉ ጥረት ሁሉ ዉድቅ ሆኗል::ወያኔ እና ከወያኔ ጋር የሚተባበሩ ሀይሎች አቶ ማሙሸት አማረ ቪዛ እንዳያገኝ ስለሚከለክሉት በተደጋጋሚ የተሞከረዉ ሙከራ ሁሉ መክኖ ቀርቷል::ይሄ በራሱ የሚነግረን በርካታ እዉነታ አለ:: ማን ምንድነዉ የሚለዉን ጥያቄ ይመልሳል::

ከወያኔ ኢፍትሃዊ ፍርድ ጋር እየተባበሩ እና ለወያኔ የተለዩ ግብ እየሰሩ የፖለቲካ ተቃዋሚ ነኝ ማለት ቀልድ ነዉ::ህጋዊ የፓርቲ አመራሮችን አሳስሮ በጠቅላላ ጉባኤ ሳይመረጡ ፓርቲዉን የምመራ ፕሬዝዳንት እኔ ነኝ ማለት አሳፋሪ ነዉ::በተለይም ምርጫ ቦርድ አቶ ማሙሸት አማረን ፕሬዝዳንት አትሆንም ብሎታል እኔን ግን ተቀብሎኛል ብሎ በደጋፊዎች ላይ መቀለድ ብሎም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ማላገጥ ወንጀል ነዉ::

5. በመሆኑም የሰሜን አሜሪካ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማህበር እነ ዶ/ር በዛብህ እየሄዱበት ያለዉን የተሳሳተ መንገድ እንዲያርሙ በጥብቅ ያሳስባል::እንዲሁም ከእነ ዶ/ር በዛብህ ጋር ለመተባበር እና ወያኔ የወሰነዉን ህጋዊ እና ጠንካራ የሆኑትን የመኢአድ አመራሮች ከፖለቲካ ዉጭ ለማድረግ የምትሰሩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ከስራችሁ መታቀብ እንዳለባችሁ ማስገንዘብ እንወዳለን:: አሁንም የመኢአድ ህጋዊ ፕሬዝዳንት አቶ ማሙሸት አማረ ብቻ ነዉ::ከኢፍትሃዊ ሀይላት ጋር እየተባበሩ ኢፍትሃዊነትን መታገል አይቻልም :: በግፍ እና በኢፍትሃዊነት የታሰሩ የመኢአድ አመራሮችን ከምርጫ ቦርድ እና ከወያኔ ጋር ተባብሮ በማሳሰር እራስን በአመራር ላይ መሰዬም ፍጹም ኢዲሞክራሲያዊ እና ጸረ ሰበአዊነት አካሄድ ከመሆንም ዘሎ ወንጀልም ነዉ:: ከወያኔ ምርጫ ቦርድ ጋር የሚተባበሩ እንዲሁም የወያኔን አዎንታዊ ፈቃድ እየተቀበሉ በህዝብ ትግል ላይ የሚቀልዱ ሁሉ ከስራቸዉ እንዲታቀቡ በግልጽ ሊነገራቸዉ ይገባል::

ከሰላምታ ጋር

ስለሽ ጥላሁን